## በዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

## ኦርቶዶክሳውያን ለቅዱሳን ለምን ይዘምራሉ? በሚል ርዕስ በቀረበው መጣጥፍ ላይ የተሰጠ መልስ

የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ብዙ ጊዜ ከሚተቹባቸው ጉዳዮች መካከል መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ፈቃዳቸው ይተረጉሙታል (አንዳንዴም እንደ ክራር እንደፈቃዳቸው ይቃኙታል) የሚል ክስ ነው። ይህንን የዲያቆን ሄኖክ ኃይሌን መልዕክት ባነበብኩኝ ጊዜ በመጀመሪያ በውስጤ የተፈጠረው ጥያቄ "ዓመድ እንዴት በዱቄት ይስቃል?" የሚል ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው። እግዚአብሔር የሰዎችን መንፈስ እያነሳሳ እና እየመራ፣ የሰው ልጅ ፈጣሪና አምላኩን የሚያውቅበትን፣ የሚጠበቅበትን ሃላፊነት እንዲወጣ እንደ መመሪያ እንዲረዳው ከሦስት ሺህ ዓመታት በላይ ወስዶ የሰጠን የሕይወት ቃል ነው። ከእግዚአብሔር ውጪ ማንም ሊተረጉመው አልተፈቀደም። ስለዚህ ኦርቶዶክስም፣ ካቶሊክም፣ ፕሮቴስታንም ብሆን መጽሐፍ ቅዱስን የሚተረጉምልኝ እግዚአብሔር እራሱ/ መንፈስ ቅዱስ/ መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ ጊዜ እ/ር መልእክቱን ባስተላለፈበት ጊዜ ለምን? ለማን? በምን ዓይነት ሁኔታ? እና የመሳሰሉትን ጥያቄ በመመለስ ወደ መልዕክቱ ጭብጥ ሃሳብ ልንደርስ ይገባናል። ማለትም የመጽሐፉን፣ የክፍሉን፣ የጥቅሱን ዓውደ ምንባብ (context) በሚገባ ማወቅ አለብን ማለት ነው። በተጨማሪም የጊዜውን የፖለቲካ፣ የመልካዕ ምድሩን አቀማመጥ፣ የኅብረተሰቡን የባህልና የአነጋገር ዘይቤም ጨምሮ ማገናዘብ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ላይ የነበረውና በወንበዴዎች ተደብድቦ በመንገድ ዳር ስለተጣለው አይሁዳዊ ክርስቶስ ምሳሌ በመስጠት ሲያስተምራቸው የነበረውን ክፍል ብንወስድ፤ የመልዕክቱ ውስጣዊ ጭብጥ ልባችንንና ሕይወታችንን የሚነካው - በዚያ ስፍራ ከሰፈረው ትምህርት በተጨማሪ ከታሪክ በኢየሩሳሌማውያንና በሰማርያ ነዋሪዎች መካከል የነበረውን የመናናቅ እና የጥላቻ መንፈስ ስንረዳ ነው። የአይሁዳዊው ወገኖች ካህኑና ሌዋዊው መርዳት ሲገባቸው ጠላት የነበረው ሰማርያዋዊው መንገደኛ እንዴት እንደረዳው ስንረዳ፣ ክርስቶስ ኢየሱስ ከእኛ የሚጠብቀው የፍቅር አገልግሎት እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ለማየት ይቻለናል። አንዳንድ ጊዜ እነዚህን የመሳሰሉትን መረጃዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ፣ ከታሪክ ማኅደሮች፣ እና ከአርኬኦሎጂ ግኝቶች የምናገኛቸው ጠቃሚ መረጃዎች ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ወጥ መጽሐፍ አይደለም። የተለያዩ የጽሑፍ ዓይነቶች ያካተተ መጽሐፍ ነው። ውብ የሚያደርገውም ይህ ነው። ትረካ አለው፣ እንደ መዝሙረ ዳዊት ሥነ-ግጥም አለው፣ የጥበብ መጽሐፍ አለው (መጽሐፈ ምሳሌ)፣ እንደነ ትንቢተ ዳንኤል እና የዮሐንስ ራእል ያሉ ደግሞ ስለ መጨረሻው ዘመን የሚገልጹ በምስልና በሲምቦል የተሞሉ ጽሑፎችም አሉት። ሁሉንም በአንድ መነጽር ማየት፣ ማንበብ፣ መረዳትና መተንተን አይቻልም። ለዚህም ጥንቃቄ መውሰድ ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ ጥንቃቄ እና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የእኛን ሃሳብና አቋም ይዘን መጥተን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ አስገብተን ሃሳባችን እና አቋማችን የሚደግፍ ክፍል በመፈለግ ትክክለኛነታችንን ለማረጋገጥ ከመሞከር መቆጠብ አለብን። የሃሰት ትምህርት መሰረት ሁል ጊዜም ይህ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጀምረን ከዚያ የምናገኘውን አቋም፤ ስነ መለኮት፣ ትምህርት፣ መመሪያ እናራምዳለን እንጂ ከውጭ ወደውስጥ አንሄድም። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንተና ዘይቤዎች በእንግሊዘኛው Exegesis (to draw out) and Eisegesis (to draw in) በማለት ይታወቃሉ።

ይህንን እንደመንደርደሪያ ካስቀመጥኩኝ ወደ ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ ምንባብ እንሂድ። ምንባቡ ረዘም ያለ እና ብዙ ሃሳቦችን ያካተተ ቢሆንም በተቻለኝ መጠን ሁሉንም ለመዳሰስ ሙከራ አደርጋለሁኝ። እንዲረዳኝም አጠር ያለ ማጠቃለያ አቀርብና ያለኝን ምላሽ አሰፍራለሁኝ። በዚህ ሂደት ውስጥ ዓላማዬ ዲያቆን ሄኖክ የሰጡት ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ እና አግባብ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትንነተና እንዳልተጠቀሙ ለማመልከት ነው።

<u>ማጠቃለያ</u>

የምንባቡ ዋነኛ እና መካከላዊ መልዕክት ለሰዎች በተለይም ለቅዱሳን ምስጋና ይገባቸዋል የሚል ነው። በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መዝሙርና ዝማሬ ውደሳ ብናቀርብላቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው የሚል አቋም ነው።

- ይህ ምስጋና እንደወትሮ አንድ ሰው አንድን ነገር ስላደረገ 'አመሰግናለሁ' ወይም ደግሞ 'እግዚአብሔር ይስጥልኝ' ማለት ይገባል ሳይሆን - በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት - አምልኮ ለእግዚአብሔር በሚሰጥበት ጊዜ ለእነዚህ 'ቅዱሳን ተብለው ለሚሰየሙ' ፍጡራን <u>መንፈሳዊ</u> ምስጋና፣ <u>መንፈሳዊ</u> ዝማሬ/መዝሙር ይገባቸዋል የሚል አቋም ነው።
- ይህም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተግባር እንደሆነ ለማሳየት ከመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ የምንባብ ክፍሎች በማስፈር ከእግዚአብሔር የተደነገገ እንደሆነ ለማመልከት ሙከራ ያደርጋል።
- ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ለምሳሌ ንጉሥ ዳዊት ለኢየሩሳሌም ዘምሯል
- መኃልየ መኃልየ እንደዚሁ ስለሰዎች የቀረበ ምስጋና ነው
- መልአኩ ገብርኤል ለማርያም ያቀረበው ሰላምታ ምስጋና ነው
- ማርያም ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል ብላለች
- ክርስቶስ እራሱ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ምስጋና ሰጥቷል
- ስለዚህ እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መነሻ እና መረጃ በማድረግ ለቅዱሳን የምስጋና መዝሙር እናቀርባለን
- በስተመጨረሻም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ - እንደ ዳንኤል 12፥3 እንደ 2ኛ ነገሥት 1፥13 እንደ ማቴ 13፥43 እና ማቴ 5፥14 እንደ ማቴ 17፥20 እና ፊሊ 4፥13 እንደ ማቴ 66፥13 እናም በመጨረሻ እንደ ቆላስያስ 2፥7 ያሉትን ምንባቦች በማጣቀስ ለሰዎች/ለቅዱሳን "መንፈሳዊ" ምስጋና መስጠት ይገባል

የሚል ትምህርት ያዘለ ጽሑፍ ነው።

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች እስመልክቼ መልስ ከመስጠቴ በፊት አንዳንድ መሠረታዊ ሃሳቦችን ላስቀምጥ።

1ኛ/ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለቅዱሳን ምስጋና ይገባል ብለው ሲሉ፣ ቅዱሳን የሚለው ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የተለየ አተረጓጎም ላይ በመመስረት ነው። ሲጀመር ቅዱስ የሚለው ቃል *ካዶሽ* ከሚለው የእብራይስጥ ቃል የተመለሰ ሲሆን ትርጉሙም 'የተለየ' ማለት ነው። እስራኤል ቅዱስ ሕዝብ ተብሎ ሲጠራ እግዚአብሔር በአብራሃም በኩል ለእርሱ ተገዢነት የለየው ሕዝብ ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን የተቀደሰ ሕዝብ በክርስቶስ ያመኑት ሁሉ ናቸው። በ1ኛ ጴጥሮስ እንደዚህ የሚል ቃል እናገኛለን "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ <u>ቅዱስ ሕዝብ</u>፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ"። ይህ መልዕክት ለተወሰኑ

ግለሰቦች የተጻፈ አይደለም ለመላው የአማኝ ኅብረተሰብ ነው። ስለዚህ ለቅዱሳን ምስጋና ይገባል ከተባለ ሁሉም አማኝ ሰው መዝሙር ሊገባው ነው።
2ኛ/ ደጋግሜ መንፈሳዊ ምስጋና የሚል ቃላት ተጠቅምያለሁኝ። ይህንን ያደረኩበት ምክንያት በኦርቶዶክስ ሥርዓት እንደዚሁም የዲያቆን ሄኖክ ጽሑፍ እንደሚያመለክተው፤ አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ፣ ወይ ዲያቆን፣ ወይ አገልጋይ አንድ ነገር አድርጎለት የሚያመሰግነው ሃሳብ አይደለም። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ ቅዱሳን አዋጥተው ገንዘብ ለኢየሩሳሌም ቤ/ክርስቲያን በማሰባሰባቸው ያመሰግናቸዋል። እነርሱም ደብዳቤ ሲልኩለት (ለምሳሌ የቆርንቶስ ቤ/ክርስቲያን ደብዳቤ ጽፋለት ነበር)። ደብዳቤው ላይ እርግጠኛ ነኝ ስለሚጸልይላቸው፣ ስለእነርሱ ስለሚያስብና ስለሚጨነቅ 'እናመሰግንሃለን' ብለው ሳይጽፉለት አይቀሩም ባይ ነኝ። ስለዚህ ምስጋና አይደለም እየተነጋገርን ያለነው። በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት ውስጥ የሚካተት እነዚህ 'ቅዱሳን' ተብለው የሚሰየሙት በሕይወትም ሆነ ከሞቱ በኋላ አሁንም ስለሚያበርክቱት መንፈሳዊ ነገሮች (ምልጃ ቢሆን፣ ጥበቃ፣ በረከት ወዘተ) ነው መመስገን ያለባቸው። ስለዚህ ለተወሰኑ ሰዎች/ቅዱሳን ነው።
3ኛ/ የኦርቶዶክስ እና የካቶሊክ እምነት እንደሚያስተምረው ከመጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ ሌሎች መጻሕፍት ለቀኖና፣ ለስነ መለኮታዊ አቋምና ድንጋጌ በጥቅም እንደሚውሉ ያምናሉ። ከዚህ በተጨማሪ ተውፊት / tradition ለሥርዓት እና አቋም መሠረት እንደሚሰጠው ያስተምራሉ።
ይህን ከሆነ ታዲያ፣ ለቅዱሳን/ለሰዎች/ለፍጡራን የምሥጋና መዝሙር መስጠት ይገባል የሚለውን ሃሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባናገኘውም (ከዚህ በታች የሚሰፍረው አስተያየት ይህንኑ ያረጋግጣል/ ያስረግጥልናል) ቢያንስ በቤ/ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በተለይም በመጀመሪያ ዓመታት ይህንን ሥርዓት ሲፈጸም ልናገኘው ይገባል። ነገር ግን እስከ 4ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ይህንን የመሰለ ሥርዓት በቤ/ክርስቲያን ውስጥ በፍጹም አናገኘውም። ይህንን በሚመለከት በሌላ ጊዜ ማብራራት ይቻላል። 'የተሻለ እውነት በደብዳቤ' በሚል ርዕስ ያሳተምኩት መጽሐፍ ይህንን በሰፊው ይገልጸዋል።

እሺ ወደ ዲያቆን ሃኖክ ኃይሌ ጽሑፍ እንመለስ።

- *መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 1 ላይ የሰፈረውን "ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ ፣ በኃጢአተኞች መንገድ ያልቆመ ፣ በዋዘኞች ወንበር ያልተቀመጠ" ምንባብ መሠረት አድርጎ ዲያቆን ሄኖክ ይህ ክፍል ለሰው ልጅ / ለቅዱሳን ምስጋና ማቅረብ ይገባል የሚል አቋም ገልጸዋል። ይህንን ክፍል ትንሽ ጠለቅ ብሎ ያነበበ እና ያጠና ሰው ከሁሉ በፊት ምስጉን ነው የሚለው ሃሳብ ወደ አማሪኛ ሲተረጎም ነው ምስጉን የሚል ሃሳብ ያዘለው እንጂ ኦሪጂናሉ የዕብራይስጥ ቃል "የተባረከ ነው" አለዚያም "ደስተኛ ነው" የሚል ትርጉም ነው ያዘለው። የምንባቡ መልዕክት የሰው ልጅ ደስታን የሚያገኘው፣ ከእግዚአብሔር በረከትን የሚያገኘው በክፉዎች ምክር ሳይታለል ሕይወቱን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ብቻ የሚመራ ሰው ነው የሚል ነው። እንደ ማስረጃ እንዲሆነን ቁጥር አንድን አልፈን ወደ ቁጥር ሁለት ስንሄድ እንዲህ ይለናል "ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል"። ስለዚህ ከምንባቡ ሃሳብ እና መልእክት ውጭ ይህ ክፍል ለሰው ልጆች ምስጋና ይገባቸዋል የሚል መልእክት በፍጹም የለውም። በተመሳሳይ ሁኔታም መዝ 32፥1 እንደዚሁ ነው። "መተላለፉ የቀረችለት ኃጢአቱም የተከደነችለት ምስጉን ነው" ሲል ይህ ሰው የተባረከ፣ ደስተኛ ነው ማለቱ ነው። አሁንም የዕብራይስጡ (መጀመሪያውኑ ሲጻፍ በዕብራይስጥ ነውና የተጻፈው) - የተባረከ፣ ደስተኛ ሰው ነው የሚል ትንታኔ ነው ያዘለው።*
  *ለማጠናከር ቢያስፈልግ ይህ ክፍል ሰዎችን/ቅዱሳንን እንድናመሰግን ይጠቁመናል እንዳንል ይህ ምንባብ ትዕዛዝ ወይም instruction አይደለም። እንደገናም ትዕዛዝ ነው የሚል ካለ ደግሞ ለተወሰኑ ሰዎች ሳይሆን በእግዚአብሔር መንገድ ለተሰማሩ ሁሉ (በዚያን ጊዜ ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ አሁን*

ደግሞ ለክርስቲያኖች ሁሉ ስለሆነ) ሁላችንም ልንመሰገን ሊዘመርልን ይገባል ማለት ነው። ሁላችንም ኃጢአታችን ይቅር ተብሎልናልና።

- ዲያቆን ሄኖክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ለምሳሌ ንጉሥ ዳዊት ለጽዮን ማለትም ለኢየሩሳሌም እንኳን ምስጋና አቅርቧል በማለት መዝ 132፥13 ጀምሮ ያለውን ምንባብ አጣቅሰዋል። አሁንም መዝሙሩ ለከተማ ምስጋና ማቅረብ ይገባል ሳይሆን የእግዚብሔርን ቃል ኪዳን የሚያሳስብ የምንባብ ክፍል ነው። እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ማደሪያው (የቤተ መቅደሱ እና የታቦቱ ማረፊያ በመሆኑ) አድርጎ መምረጡን የሚያሳሳብ ክፍል ነው። አሁን በዚህ ምንባብ ላይ ከመጽሐፉ ትንተና ውጭ የማርያምን የእምነት አቋም ይዘን መጥተን የምንባቡ ክፍል በመጀመሪያው ትርጉሙ ያልነበረውን ትርጉም ለመስጠት እንዲያመች ተደርጎ የሚቀርብ ማብራሪያ ነው። ቀደም ሲል እንዳልኩት የምንባቡ ክፍል የሚለው ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ትተን Exegesis (to draw out) እኛ የምንለውን ያረጋግጥልናል ወይ? Eisegesis (to draw in) የሚለውን ሂደት እንደተከተልን በግልጽ ማየት ይቻላል።

- መኃልየ መኃልየ ዘሰለሞን እንደዚሁ ሁለት ፍቅረኛሞች የተለዋወጡትን የፍቅራቸውን ስሜት የገለጡበትን መልእክት ተደግፎ ለሰዎች / ለቅዱሳን <u>መንፈሳዊ</u> ምስጋና በመዝሙርና በዜማ በቤ/ክርስቲያን ሥርዓት ውስጥ ማድረግ ተገቢ ነው ማለት በጣም የሚያስቸግር ይመስለኛል። የዲያቆን ሄኖክን እና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች የሚሰጡትን ትንተና ይዘን ብንቀጥል እንኳ እንደዚህ ዓይነት ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስቸግረናል። ይህ መጽሐፍ ከፍቅረኞቹ በተጨማሪ ስለ ክርስቶስ እና ስለ ሙሽራው ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚያመለክት ምንባብ ነው ብለን ብንቀጥል ክርስቶስ ለቤ/ክርስቲያን ያለውን አስተያየት/ፍቅር ሲያመለክት እና ቤ/ክርስቲያን ደግሞ ስለክርስቶስ ያላትን አስተያየት/ፍቅር የምታቀርብበት ምንባብ መሆኑ ነው። ታድያ ለሰው ስለሚቀርበው ምስጋና ከየት ነው የምናገኘው።

- ሌላው ዲያቆን ሄኖክ ያሰፈሩት ነጥብ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለማርያም የቀረበውን ሰላምታ አስመልክቶ ሲሆን፣ መልአኩ ገብርኤል ያቀረበላት ሰላምታ ዝማሬ ነውና እኛም ለማርያም ዝማሬ ማቅረብ ይገባናል የሚል ሃሳብ አስፍረዋል። በተጨማሪም ማርያም ትውልድ ሁሉ ያመሰግነኛል ብላ ማለቷ ለዚህ ድጋፍ ሰጪ ክፍል ነው ብለዋል። ከዚህ በፊት የኦሪጂናል ቃላት ትንተና እና ትርጉም እንዳመለከትኩት ጥቅሱ ያመሰግኑኛል ሳይሆን “የተባረክሽ” ወይም ደግሞ አንዳንድ ትርጉም እንደሚያሳዩት “ብጽዕት” ይሉኛል ነው የሚለው። በእርግጥም ስለ ክርስቶስ መወለድ ሲወሳ፣ ቃል ሥጋ ስለመሆኑ ሲነገርና ሲሰበክ ማርያም ከሴቶች ሁሉ ተመርጣ በመንፈስ ቅዱስ መጸነሷ በድንግልናዋም ክርስቶስን መውለዷ ለመባረኳ ያለጥርጥር ማየት የሚሳነው ያለ አይመስለኝም። ነገር ከዚህ ተነስቼ ለእርሷ መንፈሳዊ ዛማሬ ይገባታል ለሚለው አቋም እንደ መረጃም ሆነ እንደ ማስረጃ የሚያሳይ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ የቤ/ክርስቲያንን ታሪክም ሆነ ተውፊት ለሚመረምር እና ለሚያጠና ሰው ልክ እንደ ቅዱሳን አማላጅነት እና ምስጋና ለማርያምም የሚቀርበው ምስጋና እና የአማላጅነቷ ትምህርት ከ5ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በቤ/ክርስቲያን ሥርዓት ውስጥ ያልነበረ ነው። ከረፈደ ለምን ተጀመረ? እንዴትስ ተጀመረ? - ሌላ ሰፋ ያለ ውይይት የሚሻ ክፍል ነው። እንደገናም ‘የተሻለ እውነት በደብዳቤ’ በሚል ርዕስ ያሳተምኩት መጽሐፍ ይህንን በሰፊው ይገልጸዋል።

- ሌላው የተነሳው ነጥብ ክርስቶስ ለመጥመቁ ዮሐንስ ያቀረበው ምስጋና ስላለ እኛም ለዮሐንስ እንደዚሁም በዚሁ መርኅ መሠረት ለእርሱና ለሌሎች 'ቅዱሳን' ምስጋና እና ዝማሬ ማቅረብ ይገባናል የሚለው ሃሳብ ነው። ይህንን በተመለከተ ዲያቆን ሄኖክ የሉቃስ ወንጌልን ምዕራፍ 7 ቁጥር 26-28 ያለውን የምንባብ ክፍል አጣቅሰውልናል። እንዲህ ይላል "ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን? አዎን እላችኋለሁ፥ ከነቢይም የሚበልጠውን እነሆ፥ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነው። እላችኋለሁ፥ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ ማንም የለም"። ይህንን ከጠቀሱ በኋላ ዲያቆን ሄኖክ እንዲህ ብለው ጽፈዋል 'ከዚህ በላይ ምስጋና ከየት ይመጣል?"።
  ነገር ግን የቁ 28ን መጨረሻ ክፍል አውቀው ይሁን አይሁን እንጃ ለምን እንዳስቀሯት ልረዳ አልቻልኩም። ምክንያቱም "ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ ማንም የለም" ካለ በኋላ እንዲህ በማለት ይደመድማል - "<u>በእግዚአብሔር መንግሥት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል</u>"። የምንባቡን ትርጉም ወይም መልእክት ግልጽ ስለሆነ ለእናንተ ልተወው።

- በስተመጨረሻ ዲያቆን ሄኖክ ያቀረቧቸው ሃሳቦች የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለቅዱሳን ስትዘምርና ስታዜም ግጥሙን ሳይቀር የምትዋሰው ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ካስረዱ በኋላ እነዚህን ነጥቦች ያስቀምጣሉ፤
  - «ፀሐይ ተክለ ሃይማኖት ከሰማይ ሆነህ ጎብኘኝ የምንለው» - ማቴ 13፡-43 ላይ "ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ" ስለሚል ነው ብለውናል። ነገር ግን በድጋሚ አንድ ቁልፍ ሃሳብ ከጥቅሳቸው አስቀርተዋል። እርሱ ብቻ አይደለም ቀደም ሲል እንዳሳሰብኩት አንድን ጥቅስ ወስዶ እንደ ማስረጃ ከማቅረባችን በፊት በዙሪያው የሚገኘው ዓውደ ንባብ ምን እንደሚመስል አብሮ መመልከት ከስህተት ይጠብቃል። ዲያቆን ሄኖክ ያስቀሩት ቁልፍ ሃሳብ "<u>በዚያን ጊዜ</u>" የሚለውን የጥቅሱን መጀመሪያ ነው። በየትኛው ጊዜ? በመጨረሻው የፍርድ ጊዜ - እንክርዳዱ ወደ እቶኑ እሳት ሲጣል በእግዚአብሔር ትክክለኛ ትምህርት የተጓዙት (ስንዴዎቹ) ጻድቃን እንደ ፀሐይ ያበራሉ። እነዚህ ጻድቃን የተወሰኑት ብቻ አይደሉም እኛንም ያጠቃልላል። የምናበራው ደግሞ በመጨረሻው ዘመን ነው!
  - «ጊዮርጊስ ኃያል ኮከብ» መባሉ ዳንኤል 12፥3 ላይ "ብዙዎች ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ" የሚለውን ይዞ ነው ብለዋል። አሁንም ምዕራፉን ከመጀመሪያው አንስተን ስናነበው እንዲህ ይላል "<u>በዚያም ዘመን</u> ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል፤ ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ <u>የመከራ ዘመን ይሆናል</u>፤ **በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል**። በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፤ **እኵሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት**፥ እኵሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጕስቍልና። ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል፥ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ። " ከላይ በቂ ማስረጃ ስለተሰጠ መደጋገም አይስፈልግም። በመጨረሻው ዘመን የሚሆን ክስተት ነው።
  - «አቡነ አረጋዊ ሆይ ነፍሴ ዛሬ በአንተ ፊት የከበረች ትሁን» ስንል በ 2ኛ ነገሥት 1፡-13 አንድ የመቶ አለቃ በነቢዩ ኤልያስ ተንበርክኮ ያለውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ነው ተብሏል። ይህ የመቶ አለቃ ወደ ነብዩ ኤልያስ የቀረበብትን ምክንያት ማስተዋል ተገቢ ነው። ከእርሱ በፊት ተልከው የነበሩት ሁለቱ የሃምሳ አለቆች ከነሰራዊታቸው በእሳት ተበልተው ስለነበር

ይህ በንጉሱ ትዕዛዝ የተላከው ሃምሳ አለቃ፣ ሲፈራ ሲቸር የእርሱን እና የወታደሮቹን ሕይወት እንዲምርለት ያቀረበው ልመና ነው። ነፍሳችን በፊትህ የከበረች ትሁን ብሎ ሲል - ሕይወታችን ዝም ብለህ እንደተራ እንደምናምንቴ ሳትቆጥር አክብረህ ምሕረት እድርግልን ማለቱ ነው። የዕብራይስጡ ቃል - יְקַר־ – yaqar - ውድ፣ precious የሚል ትርጉም አለው። እንግዲያ ይህንን የምንባብ ክፍል ተመርኲዘን ለአቡነ አረጋዊ ነፍሴ በፊትህ የከበረች ትሁን የምንለው ነፍሳችን እንዲምሩልን ይሆን? መልሱን እናንተ እራሳችሁ መስጠት ትችላላችሁ። መረጃው ግልጽ ነው ብዬ አምናለሁኝ።

- «ገብረ መንፈስ ቅዱስ የዓለም ብርሃን ናቸው» ስንል የዓለም ብርሃን ክርስቶስ ብቻ ነው ብሎ የሚቃወም ቢኖር ራሱ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ “እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ” ብሏል። በርግጥ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ናችሁ ብሎ ለሐዋርያት ተናግሯል። የዓለም ብርሃን ሐዋርያት ብቻ ሳይሆኑ፣ ቀሳውስት ብቻ ሳይሆኑ፣ እንደ ካቶሊክ እና እንደ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የሚወሰኑት ቅዱሳን ብቻ ሳይሆኑ - የክርስቶስን ወንጌል የተቀበሉ ክርስቲያን አማኞች በሙሉ ናቸው። እንዴት? ቢባል አንደኛ ይህን ቃል ክርስቶስ የተናገረው በተራራው ስብከቱ ሲያዳምጡ እና መልዕክቱን ለተቀበሉ ሁሉ ነው። ሁለተኛ ብርሃኑ ወንጌል ነው። ይህንን መልእክት የሰማ ሰው በተራራ ላይ እንደማትሰወር ከተማ በሕይወታችን ይህንን ብርሃን ማሳየት አለብን የሚል መርኅ የሚሰጠት ክፍል ነው እንጂ ለተወሰኑ ብቻ የሚሰጥ ጸጋ አይደለም።
- «ለእመቤቴ የሚሳናት ነገር የለም» ስንል ለሚመጻደቁ መጽሐፍ ቅዱስ “እምነት ቢኖራችሁ የሚሳናችሁ ነገር የለም” እና “ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ” የሚሉትን ምንባቦች በማንበብ ለማርያም እንደዚህ ስለተባለ ከመቆጣት ይልቅ ለምዕመን የተሰጠውን እምነትና ማስተዋል ያስፈልጋል ይላሉ ዲያቆን ሄኖክ። አሁንም ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው ይህ የእምነት ስጦታ ለአማኝ በሙሉ የተሰጠ ጸጋ ነው። ለተለዩ ቅዱሳን የተሰጠ አይደለም። በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የሚገኝ የእምነት ስጦታ ነው። ታዲያ ለብቻ ተለይቶ ለማርያም ምስጋና እና ዝማሬ የሚያሰጥበት እንዴት ነው? የሆኖ ሆኖ እንደምረዳው ለማርያም የሚሳናት ነገር የለም ሲባልና አንድ ክርስቲያን የሚሳነው ነገር የለም ሲባል በውስጡ የሚያዝለው ትርጉምና ክብደት ለየቅል ሳይሆን አይቀርም።
- ዲያቆን ሄኖክ ጠርሙስን ሰብራ ሽቱን በእግሩ ላይ ያፈሰሰችውን ሴት በመጥቀስ ስለርሷ መታሰቢያ ይነገራል ብሎ ካሉ በኋላ ክርስቶስ ደማቸውን ስለ ስሙ ስላፈሰሱ ቅዱሳን ቢነገርና ቢዘመር የሚከለከል አይደለም ይላሉ። መነገር እና ስለእነርሱ ቀን ቆርጦ ለእግዚአብሔር ከሚቀርበው አምልኮ ምስጋና እና የመንፈሳዊ ሥርዓት ጋር አብሮ ተደምሮ ዝማሬ/መዝሙር ማቅረብ የተላያዩ ነገሮች ናቸው። ስለዚህች ሴት፣ ለክርስቶስ ያላትን ፍቅር ለመግለጽ ስትል ያደረገችውን በወንጌል ተጽፎ በመቀመጡ ይኸው ክርስቶስ እንዳለው እናነሳዋለን። የተቀመጠልን ደግሞ ሴትየዋን እንድናመሰግን ሳይሆን ከእርሷ ፈለግ ተምረን ለክርስቶስ ምን ያህል የፍቅር አምልኮ ማቅረብ እንዳለብን፣ ምንም እንኳን ያለንበት ሁኔታ ባይመቻችም (በዘመኗ ሴቶች በሰው ፊት/ በእንግዳ ፊት መቅረብ አይቻላቸውም ነበርና፤ ድንገትም የነበረችበት ሁኔታ ከሰው የሚያገል ስለነበር እንደዚሁም ብቃት አልነበራትምና) ክርስቶስ በትሕትና እና በተሰበረ ልብ ወደ እርሱ የመጡትን ሁሉ እንደሚቀበል ለትምህርታችን እንዲሆን እንጂ። ምንባቡን ላነበበ ደቀ መዛሙርቱ ምን ያህል እንደተቆጡ ይገነዘባል።

- በመጨረሻም መደምደሚያቸው ላይ ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ ያሳፈሩትን ጥቅስ እንመልከት። እንዲህ ይላሉ “ምስጋና እንኳን ለቅዱሳን በሃይማኖታችን ከጸናን ለእኛም ለደካሞቹ አልተከለለንም፣ እንዲህ ተብሎ ተጽፎልአልና ፦ ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታነጹ፣ እንደተማራችሁም በሃይማኖት ጽኑ፣ ምስጋናም ይብዛላችሁ!” ቆላስ 2፡-7
  አሁንም ትክክለኛውን መልእክት ለመረዳት እንዲያመች በግሪኩ የሰፈረውን ሃሳብ ማመሳከር አስፈላጊ ይሆናል። የግሪኩ ትርጉም የሚለው (የሌሎችም የእንግሊዘኛ ትርጉሞች ይህንን ያመለክታሉ) እንደዚህ ነው ‘ሥር ሰዳችሁ ታንጻችሁ፥ በተማራችሁትም እምነት ጸንታችሁ በበዛ ምስጋና ሁኑ/ኑሩ”። እናም ምስጋና ይብዛላችሁ ብሎ ሲል የአማርኛው ትርጉም ሰዎች ምስጋና ያበርክቱላችሁ ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ይሆናል። ይልቅስ በእግዚብሔር በመጽናትና በእምነት በመኖር በምስጋና የተሞላ ሕይወት ይብዛላችሁ - ማለትም ለእግዚአብሔር የሚደርስ ምስጋና ይብዛላችሁ ማለቱ ነው።

ቤተ ክርስቲያን (እንደ ድርጅት) ሆነ ግለሰብ፣ ማንም የፈቀደውን እምነት መያዝና ማራማድ ይችላል። ሰው ሲፈጠር በፈቃዱ እንዲመላለስ ተደርጎ ነውና የተፈጠረው። ክርስቶስም የስንዴውንና የእንክርዳዱን ምሳሌ ሲያስተምር ይህንኑ ነው ያስቀመጠው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ለመረዳት ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው መነሳት ያለብን እንጂ ከሰው ሥርዓት ተነስተን ማስረጃ ለማግኘት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ አንመጣም። ፍጡራንን ማመስገን፣ ለእነርሱ ጸሎት ማቅረብን፣ በምልጃቸው መተማመን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚሰጥ ትምህርት አይደለም። ቢሆን ኖሮ አይሁዳውያን ይህንኑ ሥርዓት ይፈጽሙ እንደነበር ከብሉይ ኪዳን በግልጽ እናገኘው ነበር። ወደ ሙሴ፣ ወደ አብራሃም፣ ወደ ኖኅ፣ ወደ ዳዊት የቀረበ ጸሎት ወይም ምስጋና አንዳችም ስፍራ ላይ አናገኝም። በአዲስ ኪዳን ነው የተጀመረው እንዳይባል የእግዚአብሔርን ሕልውና ሊነካ ይችላል እግዚአብሔር አይለዋወጥምና። እንደገናም በአዲስ ኪዳን እንዲያውም ቀጥተኛ የሆነ ግንኙት እግዚአብሔር አብ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መስርቷልና። ምስጋና እና ዝማሬ የሚገባው የዘላለም አምላክ ብቻ ነው።

አሜን!

ሊበን መኮንን ገብረሚካኤል
Yeteshale2014@hotmail.com
September 1st 2018
ቶሮንቶ ካናዳ

www.yeteshaleewenet.com